ANUAK JUSTICE COUNCIL

*Justice, Peace and Freedom*

# የአኙዋክ ፍትሕ ምክርቤት

*ፍትሕ፣ ሰላም እና ነጻነት*

---

# አኙዋኮች፤ በግርማዊነታቸው ዕረፍት የተሰማን ሐዘን ጥልቅ ነው!

ሕዳር 26፣ 2004ዓም

ግርማዊ ንጉሥ አዶንን አጋዳ አክዋይ ቻም የአኙዋክ ሕዝብ ንጉሥ ህዳር 20፣ 2004ዓም በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው የአኙዋክ ፍትሕ ምክርቤት (አፍም) በኢትዮጵያና በዓለም ዙሪያ ተበትነው ከሚገኙት አኙዋኮች እንዲሁም የአኙዋክ ሕዝብ ወዳጆች ጋር በመሆን የተሰማውን ጥልቅ ሐዘን ይገልጻል፡፡ ግርማዊነታቸው በሕንድና ኬንያ ሕክምና ሲደረግላቸው የቆየ ቢሆንም በመጨረሻ ላይ ከ10 ዓመት የንግሥስና ሥልጣን በኋላ በናይሮቢ ኬንያ ህይወታቸው አልፏል፡፡

የአኙዋክ ግዛት ዋና ጽህፈት ቤት በሚገኝበት በሱዳን አገር በፖቻላ አካባቢ በምትገኘው የኦታሎ ከተማ አባታቸው ከ58 ዓመታት ንግሥና በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በወቅቱ አዶንን አጋዳ በካናዳ አገር ኦታዋ ከተማ ይኖሩ ነበር፡፡ ንጉሥ አዶንን ለኮሌጅ ትምህርት የበቁ የመጀመሪያው የአኙዋክ መሪ ነበሩ፡፡ አባታቸው ሲሞቱ በንግሥናው መስመር የመጀመሪያው ተተኪ እንዲሆኑ የመረጧቸው መሆኑ ለንጉሡ ቅርበት ባላቸው ሽማግሌ የተነገራቸው ዘግይቶ ነበር፡፡ ከሚኖሩበት ካናዳ ይህንን ታላቅ ኃላፊነት ለመረከብና ወደ ደቡብ ሱዳን ደቡባዊምስራቅ ክልል ርቆ ለመሄድ በመጀመሪያ ቢያመነቱም፣ በስተመጨረሻ የወሰኑት ውሳኔ ግን ቀላል አልነበረም፡፡ በካናዳ **“A Man Who Became King”** በሚል ርዕስ በተሰራ አንድ ጥናታዊ ፊልም ላይ ይህንን ጉዳይ አስመልክተው ንጉሥ አዶንን ሲናገሩ ***‹‹መጀመሪያ ላይ አይሆንም ነበር ያልኩት፤ ምክንያቱም ይህንን ዓይነት ታላቅ ኃላፊነት ለመሸከም ፍላጎቱ አልነበረኝም፡፡ በኋላ ግን ማን ሄዶ ይረከባል የሚለው ሃሳብ አሳመነኝ››*** ብለዋል፡፡

ንጉሥ አዶንን በምዕራቡ ዓለም የለመዱትን የተቀማጠለና የተመቻቸ ህይወት በመተው ወደ ሕዝባቸው ተመልሰው፣ በአኙዋክ ለዘመናት የቆየውን ንግሥና ተቀብለዋል፡፡ በዚሁም ከአኙዋክ ነገሥታት በ23ኛው የንግሥና መስመር ላይ በመቀመጥ ሕዝባቸውን አስተዳድረዋል፡፡ ግርማዊነታቸው በሥልጣን በቆዩበት ዘመን በአኙዋክ፣ በዲንቃ፣ በኑዌርና በሙርሌ እንዲሁም በሌሎች የደቡብ ሱዳን እና የአካባቢው ሕዝቦች መካከል ሰላም እንዲሰፍን አድርገዋል፡፡ በደቡብ ሱዳን የብሔረሰቦች ምክርቤት ድረገጽ[1] ላይ ባደረጉት ቃለምልልስ **‹‹ልማት እንዲስፋፋ፣ ከአጎራባች ነገዶች ጋር የሚከሰት ግጭት እንዲቀንስ (እንዲሁም) ለሰሜን ነዋሪዎች መልካም ጎረቤት መሆን››** ከተልዕኳቸው ዋንኞቹ እንደነበሩ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም **‹‹አገርን ያክል ነገር በመከፋፈል (በመለያየት) መገንባት አንችልም፤ እኛ አንድ ሕዝብ፣ አንድ መንግሥትና አንድ ዜጋ ነን፡፡ እርስበርሳችን መስማማት አለብን››** በማለት የተናገሩት ከሚጠቀሱላቸው ንግግሮች አንዱ ነው፡፡

በግርማዊነታቸው ዕረፍት ምክንያት የተጀመሩ በርካታ ክንውኖች ተቋርጠዋል፤ በተለይ ደቡብ ሱዳን አገር ሆና ከመፈጠሯ አኳያ ጥቂት የማይባሉ መከናወን የሚገባቸው ጉዳዮች በይደር እንዲቆዩ ሆኗል፡፡ የደቡብ ሱዳን መንግሥት በቀጠናው በሂደት ሰላም እንዲፈጠርና ልማት እንዲስፋፋ፣ በአካባቢው ያሉት አኙዋኮች መብት እንዲጠበቅ ከፍተኛውን ሚና በመጫወት አዲስ ተስፋ ሊፈነጥቅ ይችላል የሚል እምነት ነበራቸው፡፡ ለዚህም ነበር ግርማዊ ንጉሥ አዶንን በአዲሱ የደቡብ ሱዳን መንግሥት ላይ ተስፋቸውን በመጣል ይህንን የተናገሩት፡- ‹‹በኅብረተሰባችን መካከል የሚፈጠር

---

[1] http://www.houseofnationalities.org/Profiles_15.asp

ማንኛውም ዓይነት አለመግባባት በመንግሥት መፍትሔ ሊያገኝ ይችላል፡፡ የደቡብ ሱዳን መንግሥት አዲስ እንደመሆኑ ጠንካራ ነው ባይባልም ወደዚያ ግን እያመራ ነው፡፡ ለዚህ ተግባር ኮሚሽነር ተመድቦልናል . . . ወደ መንግሥት በቀጥታ ያለምንም ችግር መሄድ እችላለሁ፡፡ ሬክ ማቻርን (ምክትል ፕሬዚዳንቱን) እንዲሁም ሳልቫ ኪርን (ፕሬዚዳንቱን) በቀጥታ ማግኘት እችላለሁ. . . ስለዚህ ከአሁኑ ዕድሉን ልንሰጣቸው ይገባል፡፡››

ንጉሥ አዶንጎ ከደቡብ ሱዳን ጋር ከነበራቸው ጥብቅ ቁርኝት በመነሳት ፕሬዚዳንት ኪር፣ ምክትላቸው ሬክ ማቻር እና ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናት አስከሬናቸው ከኬንያ ወደ ደቡብ ሱዳን ጁባ እንዲመጣ ከዚያም ወደ አኙዋክ ምድር በሄሊኮፕተር እንዲወሰድና የቀብር ሥነሥርዓታቸው ፖቻላ አካባቢ እንዲሆን ልዩ መመሪያ በመስጠት ተግባራዊ እንዲሆን አድርገዋል፡፡ አስከሬኑ ጁባ አውሮፕላን ማረፊያ በደረሰ ጊዜም ፕሬዚዳንቱ ከምክትላቸው ጋር በመሆን አቀባበል አድርገውለታል፡፡ አስከሬኑ ወደ አኙዋክ ምድር ከመወሰዱ በፊት በግርማዊነታቸው የክርስትና ዕምነት መሠረት በጁባ ቤ/ክ በተከናወነው የመታሰቢያ ፕሮግራም ላይ በመገኘትም በክብር ሸኝተዋል፡፡ ንጉሥ አዶንጎ ከፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪር ጋር በአንድ ት/ቤት የተማሩና ጓደኝነታቸውም ከዚያው ጀምሮ ጸንቶ የቆየ መሆኑ ብዙዎች ይመሰክራሉ፡፡

የግርማዊነታቸው መቀመጫ ከሆነው ደቡብ ሱዳን፣ ንጉሥ አዶንጎ አዲሲቷን ደቡብ ሱዳን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማምጣት እንዲሁም ለሕዝባቸው እኩልነት፣ አንድነትና ሰላም ከፍተኛ ሚና መጫወት የሚችሉበት አመቺ ወቅት ነበር፡፡ ከዚህም በላይ የአኙዋክ ሕዝብ ለዘመናት ሲደርስበት የነበረውን መፈናቀል፣ ግጭት፣ መገለል፣ መናቅ ወዘተ በውል ስለሚረዱ ችግሮቹን ከመቅረፍ አኳያ በርካታ ተግባራትን አከናውነዋል፡፡ በዚያው መጠን ያልተጠናቀቁትን የአዲስ የአመራር፣ የልማት፣ የብልጽግና ወዘተ ተግባራት የማከናወን ኃላፊነት የወደቀው በህይወት ባለነው ላይ ነው፡፡

ምክርቤታችን ያነጋገራቸው የአኙዋክ ተወላጆች በንጉሣቸው ማረፍ እጅግ ያዘኑ መሆናቸውን የገለጹ ሲሆን፤ በተለይ ግርማዊነታቸው ከአዲሱ የደቡብ ሱዳን መንግሥት ጋር በመሆን በርካታ ሥራዎችን ለማከናወን ይችሉ እንደነበር ተናግረዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ ክስተቱን ከአኙዋክ ጭፍጨፋ ጋር አገናኝተውታል፡፡ ከስምንት ዓመት በፊት አምባገነናዊው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ አኙዋኮችን ለመጨፍጨፍና አመራሩን ለማጥፋት በራሱ በአቶ መለስ ቢሮ ውስጥ ከአንድ ወር በፊት ዕቅዱ ወጥቶ ተግባራዊ የሆነው የዛሬ ስምንት ዓመት በዚሁ በህዳር/ታህሳስ ወር ነበር፡፡

የዘር ማጥፋቱ ከታህሳስ 3 — 5 1996ዓም በጋምቤላ ሲካሄድና በሺዎች የሚቆጠሩ የአኙዋክ ተወላጆች ከኢትዮጵያ ወደ ፖቻላ ሱዳን ሲሰደዱ ንጉሥ አዶንጎ ፖቻላ ተቀምጠው አስከፊ ዕልቂቱንም ሆነ ስደቱን በቅርብ ይከታተሉ ነበር፡፡ እስካሁን በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊ አኙዋኮች በፖቻላ እንዲሁም በዳዳብ (ኢፎ) ሱዳን የስደተኛ ካምፕ፣ ሌሎች ደግሞ በካኩማ ኬንያ የስደተኛ ካምፕ ይገኛሉ፡፡ ደቡብ ሱዳን ነጻነቷን ከተጎናጸፈች በኋላ ቀጣዩ ተግባር በኢትዮጵያ የሚገኙትን አኙዋኮች የሚመለከት መሆኑን በመግለጽ ንጉሥ አዶንጎ ‹‹(አሁን) ችግሩ ያለው ከኢትዮጵያ በኩል ነው፤ እኛ ስለነዚህ የድንበር ማካለያዎች ምንም የሚያገባን ነገር የለም›› ብለው ነበር፡፡ እንደእውነቱ ከሆነ ቅኝ ገዢዎች የአኙዋክን ምድር ለሁለት ከፍለው የወሰን መስመር ያደረጉ ቢሆንም የአኙዋክ ግዛት ግን በአንድ የንጉሥ አስተዳደር ሥር የሚገኝ ነው፡፡

ግርማዊነታቸው በኢትዮጵያ የሚገኙት አኙዋኮች በዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ከተካሄደባቸው በኋላ አሁን ደግሞ ህወሃት/ኢህአዴግ ለምና በውሃ ኃብት የበለጸገውን ‹‹መሬታቸው እየነጠቀ›› ለካሩቱሪ የሕንድ ኩባንያ እንዲሁም ለአላሙዲ፣ ለሳውዲ ስታር ድርጅትና ለሌሎች የሥርዓቱ አቀንቃኞች በመስጠት ነዋሪውን ለስደት እየዳረገ መሆኑን በመከታተል የአኙዋኮች የስደት ካምፕ ኑሮ ያበቃ ዘንድ በከፍተኛ ሥራ ተጠምደው ነበር፡፡ በሱዳን የእርስበርስ ጦርነት ወቅት እርሳቸው አገር ለቅቀው ወደ ካናዳ ከመምጣታቸው በፊት በኩባ ለሦስት ዓመታት በስደት በመኖራቸው የስደተኝነትን ሕይወት በውል ስለሚረዱ ለስደተኞች ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ አድርጓቸዋል፡፡

በዓለም ዙሪያ የምንገኝ አኙዋኮችና ወዳጆቻችን በንጉሥ አዶንጎ ኅልፈት እጅግ መራራ ሐዘን ቢሰማንም እርሳቸው የጀመሩትን የሰላም፣ የልማት፣ የፍትሕና የነጻነት ዓላማ በማንገብ ለተግባራዊነታቸው በጽናት ልንቆም ይገባናል፡፡ ግርማዊነታቸው ንግሥናቸውን ለመቀበል ባመነቱበት ወቅት ‹‹. . .እኔ ካልሄድኩ ማን ሄዶ ይረከባል›› እንዳሉት ሁላችንም ተመሳሳይ ጥያቄ ራሳችንን ልንጠይቅ ያስፈልጋል፡፡ የንጉሥነትን ሥልጣንና ኃላፊነት የሚወስደው አንድ ሰው ብቻ ቢሆንም ሌሎቻችንን ግን በግል ልናደርግ የምንችለውን ሁሉ ከማድረግ ወደኋላ ማለት የለብንም፡፡

ለንጉሥ አዶንጎና ለግርማዊነታቸው ቤተሰቦች እንዲሁም ለመላው አኙዋክና የአኙዋክ ወዳጆች እግዚአብሔር ብርታትን፣ መጽናናትንና ጥንካሬን እንዲሰጣቸው እንመኛለን፡፡ በተለይ በዚህ የሐዘን ወቅት ንጉሥ አዶንጎ ያምኑና ይተማመኑ በነበረው እግዚአብሔር እኛም እምነታችንን በማድረግ እንጽና፡፡ ፈጣሪ አኙዋክን ይባርክ፤ በአካባቢው ለሚገኙቱ ሁሉ በረከት አድርጎት በታላቁ ጌታ ቅዱስ ተራራ ላይ የምስጋና መባን ለመሰዋት ያብቃን!!

# የአኙዋክ ፍትሕ ምክርቤት

ለተጨማሪ ዝርዝር ማብራሪያ የአኙዋክ ፍትሕ ምክርቤት (አፍም) ዋና ሊቀመንበር አቶ ኦቻላ አቡላን በስልክ +1 (604) 520-6848 ወይም በጾዳቤ፡ Ochala@anuakjustice.org ማግኘት ይቻላል፡፡

ይህንን ሪፖርት ለማጠናከር የረዱንን፡ አቶ ኦቻላ፣ አቶ ኡጁሉ፣ አቶ ኦጆይ፣ አቶ ኦባንግ ጆቢ (ፎቶግሮቹን ያነሳው) እና ሌሎቹንም የምክርቤታችንን ባልደረቦች እናመሰግናለን፡፡ የግርማዊነታቸውን የቀብር ሥነሥርዓት የሚያሳዩትን ምስሎች ከዚህ በታች እንዲመለከቱ እንጋብዛለን፡፡




## ግርማዊ ንጉሥ አዶንጎ አጋዳ

## 1952 - 2004



ሕዝቡ ለአቀባበል ወደ አየር ማረፊያ ሲያቀና






በአቀባበል ሥነሥርዓቱ ላይ የተሰበሰበው ሕዝብና ከፍተኛ የሱዳን መንግሥት ባለሥልጣናት







የደቡብ ሱዳን ምክትል ፕሬዚዳንት በአውሮፕላን ማረፊያው ሲደርሱ አቀባበል ሲደረግላቸው








**የግርማዊነታቸው አስከሬን ወደ ጁባ ሲጓጓዝ**



**የደቡብ ሱዳን ፕሬዚዳንትና ምክትላቸው በተገኙበት የቤ/ክ አገልግሎት ሲካሄድ**

**የቤ/ክ አገልግሎት ከተጠናቀቀ በኋላ ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪርና ምክትል ፕሬዚዳንት ሬክ ማቻር ከሐዘንተኛው ጋር የመሰነባበቻ ቃል ሲለዋወጡ**



**የመጨረሻ ስንብት**



**የቤ/ክ አገልግሎት ከተጠናቀቀ በኋላ ፕሬዚዳንት ሳልቫ ኪርና ምክትል ፕሬዚዳንት ሬክ ማቻር ከሐዘንተኛው ጋር የመሰነባበቻ ቃል ሲለዋወጡ**




# ግርማዊ ንጉሥ አዶንጎ አጋዳ

1952 - 2004